# "በመስተዋት ቤት የሚኖር ሰው ድንጋይ ለመወርወር የመጀመርያ መሆን የለበትም"!

ከግርማይ ገዛኸኝ

አስቅድሜ፤ ይህ ከላይ በርእስነት የተጠቀምኩት የአነጋገር ዘይቤ የተወሰደው ከባዕድ አባባል መሆኑ እንዲታወቅልኝ አንባቢን ለማስታወስ እወዳለሁ። ያም ሆኖ ለጊዜው በዚህ ጽሑፍ ውስጥ መስተዋቱ ውስጥ ያለውን ዝርዝሮ የማቅረብ ዓላማ ያነገበ አይደለም። ሆኖም፤ ርእሱን ለመጠቀም አቶ ሥዩም በርሀ ለአቶ በየነ ገብራይ በIDA FB የሰጡትን መልስ ሳነብ ስለ ኢ.መ.ተ.ማ (IRAA) የሰጡት የተሳሳተ ትንተና ማስተካከያ ሊሰጥበት እንደሚገባ ስላመንኩበት ይህንን ርእስ ለመጠቀም ተገድጃለሁ። እላይ በገለጽኩት ምክንያት የዚህ መጣጥፍ ዋና ይዘት፤ በተጠቀሰው FB የሰፈረውን አጭር መጣጥፍ ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ለጊዜው ብዙ ዝርዝር ውስጥ ከመግባት ለመቆጠብ ስለምፈልግ ነው። ምናልባት ዝርዝር ውስጥ ለመግባት የምገደድበት ሁኔታ ከተፈጠረ ግን በሰፊው ልሄድበት እንደምችል አንባቢን ማሳሰብ እወዳለሁ።

በማስቀደም አቶ በየነ ገብራይና አቶ ሥዩም በርሀ ከዚህ በፊት የተለዋወጧቸውን ውይይቶች ለመከታተል አለመቻሌን ለማሳወቅ እወዳለሁ። ሆኖም፤ ምንም ይለዋወጡ ምን አሁን አቶ ሥዩም ኢ.መ.ተ.ማን በሚመለከት ያቀረቡት ሃተታ መልስ እንደሚያስፈልገው አምኘበት አለሁ። እነዚያን የተለዋወጡዋቸውን ሓሳቦች አለማንበቤ እኔ የምወክለው ማህበር ኢ.መ.ተ.ማን (IRAA) ከመከላከል የሚያግደኝ አይሆንም። መልሴን የአቶ ሥዩም ጽሑፍ በተነበበበት ፎረም ለማቅረብ ብችል ኖሮ፡- የሳቸውን ጽሑፍ ያነበበ ሁሉ የኔንም መልስ ለማንበብ ዕድል ይገጥመው ነበር። ይህ አሠራር ለመከተል ተችሎ ቢሆን ኖሮ አንባቢ፤ የሁለታችንም ጭብጦች ለማገናዘብ ስለሚረዳው ትክክለኛ መስሎ ያገኘውን ሓሳብ የመደገፍ ዕድል ያገኝ ነበር። ሆኖም፤ ከላይ በተጠቀሰው ፎረም ላይ አመለካከቴን ለማስፈር ዕድሉን ስለተነፈግኩ፤ አማራጭ መንገድ ለማፈላለግ ተገድጃለሁ። በተጠቀሰው ፎረም በአቶ ሥዩም ጽሑፍ ሥር በሚገኘው አስተያየት መስጫ ሳጥን ውስጥ ልክ እንደሌሎች አስተያየት ሰጪዎች እኔም "he who lives in a glass house shouldn't be the first to throw stones" የሚል አስፍሬ ነበር። የፎረሙ አስተዳዳርዎች አስተያየቴን ለይተው ሲያነሱት እኔን አስተያየት እንድሰጥበት ያነሳሳኝ ጽሑፍ ግን አልተነሳም ነበር። ተመልሼ የኔን አስተያየት ነጥሎ ማንሳት በአሰራር ደረጃ ስሕተት ሆኖ እንዳገኘሁት ለጠፍኩ። እሱንም ነጥለው አወጡት። ከዛ በኋላ ልሳተፍበት የማይፈቀድልኝ FB ፎረም ውስጥ ቦታ መያዙ አስፈላጊ ሆኖ ስላላገኘሁት ከቡድኑ ራሴን ለማውጣት ተገድጃለሁ! ቦታው እንዲሰፋላቸውም እመኝላቸዋለሁ።

ስለፎረሙ ያንን ካልኩ ዘንዳ ወደ ተነሳሁበት ርእስ ልመልሳቹህ። እውነቱን ለመናገር ይችን መጣጥፍ ለማቅረብ በመገደዴ እጅጉን አዝናለሁ። ሆኖም ግን እምነህበት ለማሳካት የምትሯሯጥለት ዓላማህና እምነትህ በተራ አሉባልታና ስም ማጥፋትና የተሠራውን መልካም ነገር ለመናድ ሲሞከር ዝም ብሎ እንደማነኛው ተመልካች/አንባቢ አይቶ ማለፍ ምንነትህንና አንተነትህን አሳልፎ ከመስጠት ተለይቶ የሚታይ ሆኖ አላገኘሁትም። በመሆኑም፤ ብዙ ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ ኢ.መ.ተ.ማን አስመልክቶ በተሰነዘረው ውንጀላ ላይ ያለኝን ተቃውሞ ለማቅረብ ተገድጃለሁ።

ወደ አቶ ሥዩም በርሀ ጽሑፍ ይዘት ከመግባቴ በፊት ይህንን ጽሑፍ ለመለጠፍ ያስገደዳቸው ሁኔታን በጣም ባጭሩ መዳሰስ እፈልጋለሁ። እዚህ ላይ ኢ.መ.ተ.ማ እንዴት ተመሠረተ፤ እነ አቶ ሥዩም በኅዳር 2009 ዓ.ም.ፈ ጠርተውት የነበረው የስልክ ስብሰባና ያኔ የተቋቋመው ኮሚቴ በኢ.መ.ተ.ማ ምሥረታ ላይ የነበረው ተጽእኖ ምን ነበር?.....ወዘተ የሚሉና ሌሎች በርካታ ጉዳዮችን አንስቶ ለመተንተን ጊዜው አይበቃንም። በመሆኑም እዘለዋለሁ። አቶ ሥዩም ገና ኢ.መ.ተ.ማ ይፋ እንደሆነ ይመስለኛል ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ከፍተኛ የሆነ አቧራ እንዳስነሱ የምናስታውሰው ነው።

ኢ.መ.ተ.ማን ለመቃወም አቶ ሥዩምና የተወሰኑ ጓደኞቻቸው ስንት የስልክ ስብሰባ በአቶ ሥዩም በራሳቸው ሊቀመንበርነት እንደተካሄደ የማውቀው ነው። ስለሆነም፤ የዛሬ ጽሑፋቸው የነዛ ስብሰባዎች ተቀጥላ እንጂ ለብቻ ተለይተው የሚታዩ አይደሉም። በመሆኑም፤ የአቶ ሥዩም የዛሬ ጽሑፍ ይዘት ያኔም ይዘዉት የነበረ አቋም ቀጥተኛ ነጸብራቅ ነው። ስለሆነም፤ ዛሬ ሽፋፍነው ለማቅረብ የሞከሩትም የዛን ጊዜ አቋማቸውን ነው። ለፖለቲካ ጀማሪ ነኝ ያሉት እንዳለሆኖ ኢ.መ.ተ.ማ የፖለቲካ ድርጅት እንዳልሆነ የመለየት አቅም ያንሳቸዋል ብዬ ለማመን ከብዶኛል። በተቃራኒው እንዳየውም እገደዳለሁ። አቶ ሥዩም አባል መሆን አለመሆናቸውን መናገር ባልችልም፤ የተሓህት/ኢህአዴግ ፖለቲካ አቀንቃኝ ለመሆናቸው የሚያጠያይቅ አይደለም። በመረጃም ሊደገፍ የሚችል እውነት ነው። በተቃራኒው ኢ.መ.ተ.ማ እንደ ማኅበር ሲቪክ ማኅበር ነው። የፖለቲካ ድርጅት ለመሆን ቢፈልግ የመሆን መብት ኢትዮጵያ ውስጥ በሕገ-መንግሥት የተደነገገ ጉዳይ ነው። ኢ.መ.ተ.ማ ግን የፖለቲካ ድርጅት መሆን ሳይሆን የመረጠው የመብት ተሟገች መሆኑን ነው። ለኢሮብ ህዝብ መብት ይሟገታል። ሲሟገት እሳቸው የሚያምኑበት የተሓህት/ኢህአዴግ ፖለቲካን ስለማይለማመጥ አሳብበው በጠላትነት ለመፈረጅ ስለፈለጉ እንደሆነ ላሰምርበት እፈልጋለሁ። ባይሆን ኖሮ፤ ከዚህ ቀጥለው የሚነሱ ነጥቦች በተጠቀሰው ፎረም የሚያሰፍሩበት ምንም ምክንያት ሊኖር ባልቻለ ነበር። ስለዚህ አቶ ሥዩም የራሳቸው የፖለቲካ ተልእኮ ባይኖራቸው ኑሮ አጭሰው ጨርሰው የረገበ አቧራን ዛሬ ማንሳት ባልተገባቸው ነበር። ይህንን እዚህ በመቅጨት ወደ ርእሰ ጉዳዩ ልመልሳቹህ።

አቶ ሥዩም በጽሑፋቸው ውስጥ ኢ.መ.ተ.ማ እያላቹህ የምትጠሩት ማኅበርና ከዚህ ማኅበር አንጻር ያለው የፖለቲካ ትርጉም በሚመለከት ለመወያየት ላለመግባባት ተግባብተን እንቀጥል ብሏል። እዛው በዛው ባያፈርሱት ኑሮ፤ ብዙ መልስና እንካ ስላንትያ ውስጥ መግባት ባላስፈለገን ነበር። ይሁን እንጂ የፖለቲካ ቡድንን መግለጽ እጅጉን እንደሚከብድና፤ ሆኖም ይህ መድረክ ቦታው ስለማይሆን እዚህ ላይ ወደ ክርክር እንደማይገቡ ይገልጻሉ። አስከትለውም፤ እሳቸው የታሪክ ሙሁር እንደመሆናቸው ፖለቲካን በሚመለከት ዕድሜአቸውን ሙሉ በፖለቲካ ካሳለፉት አቶ በየነ ጋር ሲነጻጸር ገና ጀማሪ መሆናቸውን በራሳቸው ላይ ይመሰክራሉ። ስለሆነም ይሉናል አቶ ሥዩም፤ የፖለቲካ ትንተናውን ለአቶ በየነ ገብራይ በመተው አንባቢ የራሱን ፍርድ እንዲሰጥ ይማጸናሉ። እዚህ ላይ “ዝአኸለንያ ጢሒነንስ፤ በዓለ ማርያም ይብላ” የሚለውን የትግርኛ ምሳሌ አስታወሰኝ።እዚህ ላይ አቶ ሥዩም ኢ.መ.ተ.ማ የፖለቲካ ቡድን ነው የሚለው ሙግታቸውን ላንባቢ ለማስጨበጥ የሞከሩት በተራ ብልጣብልጥነትና በገደምዳሜ ነው። “እኛም አውቀናል፣ ጉድጓድ ምሰናል” አሉ አይጦች ነው የሚባለው!

በመጀመሪያ ደረጃ “የታሪክ ተማሪ ስለሆንኩ ፖለቲካን በሚመለከት ተለማማጅ/ጀመሪ ነኝ” ማለታቸው ስሕተት አለበት። ገና የፖለቲካ ጀማሪ/ተላማጅ ነኝ የሚለው ግን ቅቡል ሊሆን ይችላል። ይህንን ቅቡል የሚያደርገው የታሪክ ተማሪ ስለሆንኩ የሚለው አባባል ግን ውኃ የሚቋጥር ምክንያት አይደለም። በፖለቲካ ሕይወት አልፈው የዓለማችንን ገጽታ የቀየሩ በርካታ የታሪክ፣ የተፈጥሮ ሳይንስ፣ የሕግ፣ የፍልስፍና፣ የኢኮኖሚ.....ወዘተ ተማሪዎች እንደነበሩና እንዳሉ ለመካድ የሚቻል አይሆንም። ስለሆነም፣ ራሳቸው እንደመሰከሩት የፖለቲካ ጀማሪ የሆኑት የታሪክ ተማሪ ስለሆኑ ሊሆን አይችልም። የታሪክ ተማሪ መሆን ፖለቲካን ላለመተንተን ምክንያት ሊሆን አይችልም። አቶ ሥዩምም ቢሆኑ በዚች አጭር ጽሑፋቸው ውስጥ ፖለቲካን አልተነተንኩም ካሉ ሌላ ችግር ይኖራል ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርሰን ይችላል። የሆነ ሆኖ ይህንን ባጭሩ እዚሁ እንቋጨውና አንባብዎች አብራቹሁኝ ዝለቁ!

በመቀጠል የኢ.መ.ተ.ማን አዎንታዊና አሉታዊ ጎኖች ከአገር ውጭም ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚኖረው የኢሮብ ማኅበረሰብ አንጻር አንሰተን ከብቶች ቤት እስኪገቡ ድረስ መከራከር እንችላለን ይሉናል። ሆኖም፤ ከጉዳቱም ሆነ ከአሉታዊ ጎኑ አንጻር በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ከሚገኘው

ኅብረተሰባችን በመ.ኢ.ተ.ማ ምክንያት የደረሰው ጉዳትም ሆነ ጥቅም አልጠቀሱም። የቀረበው ጽሑፍ ከሚገለጽባቸው ደካማ ጎኖች አንዱም ይኸው ነው። ሥዩም በዚህ ጽሑፋቸው ውስጥ ያቀረቧቸው ውንጀላዎች በቀላሉ የሚታለፉ አይደሉም። የኢ.መ.ተ.ማ ዓላማዎች የህብረተ-ሰባችን ሁለገብ እድገት ሊያመጡ ይችላሉ ተብለው የተቀረጹ ናቸው። በዚህ ላይ አቶ ሥዩምም ቢሆኑ ጥርጣሬ ያላቸው አይመስልም። ቢኖራቸው ኖሮ ኢ.መ.ተ.ማን በደፈና ከመወንጀል ተቆጥበው፣ የማይጠቅሙ፤ የማይረቡ የሚሏቸውን የኢ.መ.ተ.ማ ዓላማዎች ላይ በማትኮር ኢ.መ.ተ.ማን አፈር ሊያስግጡ በቻሉ ነበር። ያንን ለማድረግ ቢችሉ ኖሮም ሁላችን እናደንቃቸው ነበር፤ ውይይቱም ከተለመደው አሉባልታ ወጥቶ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በተቻለ ነበር። የአሁኑ ዓይነት ተራ ውንጀላ መወርወር ግን የውይይቱን ደረጃ ያወርዷል። የውይይት ደረጃችን መውረድ ደግሞ የሚያስከትለው የጋራ ውድቀታችንን ይሆናል። በዚህም፣ እንደ የኅብረተ-ሰብ ውድቀት ወይም እድገት (የተኛውን ለማለት እንደፈለጉ በግልጽ ማስቀመጥ ስለተሳናቸው፤ በገደምዳሜ የሰፈረውን እንደ አቋም ለመውሰድ አልመረጥኩም) የሚመለከት በመሆኑ ገንቢውም ሆነ አሉታው ጎኖች ተፍረጥርጠው መቀመጥ ነበረባቸው ብዬ አምናለሁ። ሓሳቦች መቅረባቸው ካልቀረ ተልፈስፍሰውና በገደምዳሜ ሳይሆን፤ ቁልጭ ብለው ነጥረው ወጥተው መቅረብ አለባቸው ብዬ አምናለሁ። የዚህ ዓይነት አቀራረብ የተሳሳተው ስሕተቱን በመጠቀም ለማረም ዕድል ያገኛል። በመሆኑም፤ ጉዳቱም ሆነ ጥቅሙ ተለይቶ መቅረብ ይገባው ነበር። ድፍን ያለ መጨበጫ የሌለው ሆኖ ሓሳብ በማቅረብ  አንባቢ ይፍረደው ማለት መሳቅያ ከመሆን የሚዘል ካለመሆኑም በላይ ለጻፍከው ስንክሳርና ፈጠራ ሓላፊነት ለመውሰድ አለመፈለግን ወይም አለመድፈርን ያመላክታል። ያለውን እውነት እንዳለ ቁልጭ አድርጎ ለማስቀመጥ ድፍረት ይጠይቃል። ካልሆነ አላስፈላጊ ቅራኔ ከመጋበዝ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም።

ቀጥለውም፤ አቶ ሥዩም በረሀ፣ ኢ.መ.ተ.ማን አስመልክቶ የተለያዩ ሰዎች ከሚከተሉት አንዱ(either/or being ይሉታል) አፍራሽ የፖለቲካ ቡድን፤ የተዋጣለት የመብት ተሟጋች ቡድን፤ ምንም ሓላፊነት የማይሰማው የጠላውን ለማጥቃት ወደ ኋላ የማይል ሥርዓት አልበኛ ቡድን ወይም በቤተ-ሰብነት ጠባብ አመለካከት የተመረዘ፤ አጉል ዝና ፍለጋ የሚሯሯጥ ቡድን፤ (ሰረዝ የኔ) በሚለው ላይ እያንዳንዱ የራሱ ግንዛቤ እንዲሰጥበት የሚተው ነው ይላሉ።

ነገሩን አንድ ባንድ ዘርዝሮ ማየት ጠቃሚ ይሆናል። አቶ ሥዩም "አፍራሽ የፖለቲካ ቡድን፤ የተዋጣለት የመብት ተሟጋች ቡድን፤ ምንም ሓላፊነት የማይሰማው የጠላውን ለማጥቃት ወደ ኋላ የማይል ሥርዓት አልበኛ ቡድን ወይም በቤተ-ሰብነት ጠባብ አመለካከት የተመረዘ፤ በሌሎች የመታወቅ ፍላጎት የተጠናወተው ቡድን፤" ብለው የማመን መብት አላቸው። ይህ መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል ብዬ አምናለሁ። ግን አንድ ሊታለፍ የማይገባውና የሓላፊነት ስሜት ሊጎድለው የማይገባ ጉዳይ አለ! ይህም፤ የሚቀርበው ውንጀላና ስም የማጥፋት ዘመቻ፤ በማስረጃ፣ በጭብጥ፤ በመረጃ.......ወዘተ የተደገፈ፤ በአመክንዮ ሊደገፍ የሚችል መሆኑን የማረጋገጥን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት ይጠበቅበታል። ሆኖም ግን፤ በአቶ ሥዩም በረሀ የቀረበው ውንጀላና ስም ማጥፋት ውንጀላውን በተጨባጭ ማስረጃና ጭብጦች የተደገፈ ባለመሆኑ፣ የተወሰኑ በስሜት የሚነጉዱና ነገሮችን በሚዛን ላይ አስቀምጠው የመመርመር ዓቅም የሚጎድላቸው የተወሰኑ የዋሆችን አእምሮ ከመበረዝ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም። ነገሮችን አብጠርጥረው የማየትና የመገንዘብ አቅም ያላቸው ሓላፊነት የሚሰማቸው በርካታ ወገኖች መኖራቸውን መዘንጋት የኋላ ኋላ ለቅሌት እንደሚዳርግ ግን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ኢ.መ.ተ.ማ የፖለቲካ ቡድን ነው ወይስ አይደለም የሚለውን የምንመልሰው አቶ ሥዩምና እኔ ሳንሆን በጽሑፍ ሰፍረው ለህዝብ ይፋ የተደረጉ፤ ለተግባራዊነታቸው በተቻለኝ ዓቅም እንቀሳቀሳለሁ ብሎ ይፋ ያደረጋቸውና የሚከተላቸው ዓላማዎች ናቸው። ስለሆነም፤ ኢ.መ.ተ.ማ መተቸት ካለበት በዓላማዎቹ ብቻና ብቻ ይሆናል። ይፋ ያደረጋቸው ዓላማዎቹን አብጠርጥሮ መተቸት ይቻላል፤

ይገባልም። ከሚቀርቡ ገንቢ ትችቶች የሚጠቀመው ኢ.መ.ተ.ማና በዛም መጨረሻ ላይ መላው ሕብረተ-ሰባችን መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም። ስለሆነም፤ በኢ.መ.ተ.ማ ዓላማዎች የሚታያቸው ግድፈት ካለ ሳይሸፋፈን፤ በግልጽ ነጥብ በነጥብ ቀርቦ ልንወያይበት እንችላለን። ኢ.መ.ተ.ማን የፖለቲካ ድርጅት የሚያደርገው ጭብጥ ካለም አንቀጹን ጠቅሶ በግልጽ ቀርቦ ህዝብ እንዲወያይበት ማድረግ የሕብረተ-ሰባችንን የአስተሳሰብ አድማስ ስለሚያሰፋና ኢ.መ.ተ.ማም ስሕተት ካለበት ለማረም ስለሚረዳው እጅጉን ጠቃሚ ነው፤ ያቅርቡት። ለመሆኑ፤ የፖለቲካ ድርጅት ቢሆን ወንጀሉ ምኑ ላይ ይሆን? **የተዋጣለት የመብት ተሟጋች ቡድን?** ኢ.መ.ተ.ማ የተዋጣልኝ ነኝ የሚል እምነት ለመያዝ በመሥራት ላይ ቢሆንም የተዋጣልኝ ነኝ አይልም። አቅሙ በፈቀደለት መጠን ግን በኢሮብ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን የመብት ገፈፋን አስመልክቶ የአቅሙን በማድረግ ላይ እንዳለ ወለል ብሎ የሚታይ ሃቅ እንጂ ድብቅ ሚስጢር አለመሆኑ ግልጽ ነው። ካስፈለገም በጭብጥ አስይዞ መከራከር ይቻላል።

**የጠላውን ለማጥቃት ወደ ኋላ የማይል ሥርዓት አልበኛ ቡድን?** ትክክለኛ መልሱ አይደለም ነው። ኢ.መ.ተ.ማ የአመለካከት እንጂ የሰው ጠላት አለኝ የሚል እምነት የለውም፤ አይኖረውምም። በአስተሳሰብ ልዩነት ላይ የራሱን አመለካከት ማስፈር ግን የማይገሰስ መብቱ ነው። ኢ.መ.ተ.ማ በጥላቻ የሰው ስም የሚያጠፉ ማኅበርም አይደለም። ኢ.መ.ተ.ማ ስሜን በጥላቻ አጉድፏል የሚል ካለ ጭብጡን ይዞ ቢቀርብ፣ ይቅርታ ለመጠየቅ ከልብ የሚተጋ ማኅበር እንጂ በትዕቢት ተወጥሮ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚል ልበ ደንዳና አይደለም። ለመሆኑ ግን አቶ ሥዩም የአንድ ተበዳይ ስም በመጥቀስ የክሳቸው ተአማኒነት ሳያስረግጡ እንደዚህ ዓይነት ወሳኔ ላይ ለመድረስ እንዴት እንደቻሉ ማብራራትን ረስተውት ይሆን ወይስ የሚያቀርቡት ጭብጥ ስለሌላቸው? መልሱን ከሳቸው እጠብቃለሁ!

“**ሥርዓት አልበኛ ቡድን**”? በማለት ያቀረቡትም ቢሆን፤ የሥርዓት አልበኝነት መስፈርቶችን ካለመገንዘብና ትክክለኛ ትርጉሙን ካለማወቅ የመጣ ይመስላል። “ደርግ ሥርዓት አልበኛ” የሚል ስድብ ይጠቀም ስለነበረ ብቻ መድገሙ የትም አያደርስም። በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ የሥርዓት አለብኝነት መሥፈርቶችን ለመተንተን አይከጅለኝም። በዚህ ዓይነት ነገ “ሽብርተኛ” የሚል ቅጽል ተይዞ እንደማይመጣ ዋስትና የለም። የሆነ ሆኖ ኢ.መ.ተ.ማ በሥርዓት አልበኝነት የሚያስከስስ ባህሪ እንደሌለው አስምሬበት ለማለፍ እወዳለሁ።

“.... **በቤተሰብነት አባዜ የተለከፈ ቡድን**”? መቼም የዘበኑ ነገር ሆነና ሰዉ ምንም ዓይነት ጭብጥ ሳያይኖረውና ሳያቀርብ እንደፈለገ የሌላውን ስም ለማጥፋት ወደኋላ የማይልበት ዘመን ላይ ደርሰናል። እረ ባካቹህ ወገኖቼ ለማንም ስለማይጠቅምና በማኅበራዊ ሕይወታችንም የከፋ አደጋ ሊደቅን ስለሚችል ጥንቃቄ የማድረግ ሓላፊነት ይኑረን! የተባለው ዓይነት የማህበረ-ሰባችንን ህልውና የሚጋፋ ጠባብ የቤተ ሰብነት ስሜት ካለ ደግሞ በፍርሓት መሸበብ የለብንም። በግልጽ እናውጣው፤ በመተፋፈር ወይም በመፍራት የጋራ ቤታችንን የሚያፈርስ ጉድ አለ ከተባለ ከነጭብጡ ይቅረብ፤ እንወያይበት፤ መፍትሔው ማዶ ለማዶ ቆሞ በመፎካከር ተኳርፎ መቀመጥ ሳይሆን በግልጽ ተቀራርቦ መወያየት ላይ ነው ያለው፤ አቶ ሥዩምም እነደጀመሩት አለ የሚሉትን ጠባብ የቤተ-ሰብነት አባዜ በግልጽ በማጋለጥ እዳር የማድረስ ሓላፊነት እንዳለባቸው ቢያውቁት መልካም ነበር። በመረጃና ማስረጃ የሚደገፍ ጉዳይ ካለ እንምከርበት እንወያይበት። ኢ.መ.ተ.ማን በሚመለከት ግን አቶ ሥዩም የቤተ-ሰብነት ጠባብ ፍላጎት የተመረዘ መሆኑን የሚያስረዳ ቅንጣት ማስረጃ ማቅረብ እንደማይችሉ በልበሙሉነት ለመናገር እችላለሁ። የኢ.መ.ተ.ማ አባሎች የአገራቸውና የህዝባቸው ደህንነትና እድገት የሚያንገበግባቸው የህዝብ ወገኖች እንጂ የቤተ-ሰብ ጠባብ ፍላጎት ለማርካት የተሰባሰቡ ፈጽመው አይደሉም። ለዚህም፤ ጭብጥ ማቅረብ አቶ ሥዩም ፈጽመው አይችሉም። ከቻሉ ደግሞ ሜዳውንም ፈረሱንም ይኸው ጀባ ቢያቸዋለሁ።

“…… ከሌሎች ዝና ለመቸር የሚሠራ ቡድን”? ይህ ትንሽ ያስቃል! በትግርኛ “ናታስያ ንሓማታ” የሚል ቢሂል አለ። ኢ.መ.ተ.ማ ዝና ለማትረፍ የተቋቋመ ማህበር አይደለም። ዝና ለማግኘት ብሎ በየትም በተወደረ ካሜራ ፊት ለመቆም የሚራወጥ ማህበርም አይደለም። ዓላማ ይዞ የተነሳ ነው። ዓላማዎቹም በዝና የሚከናወኑ እንዳልሆኑ ጠንቅቆ ያውቃል። ስብእናን ለማግዘፍ በሚደረገው ውድድር ውስጥም አይገባም አያስፈልገውምም። በዚህ በኩል ልምድ ለመቅሰም ለጥያቄ የሚያቀርበው ማመልከቻም እንደማይኖር ቃል መግባት ካስፈለገ ቃል እንደሚገባ እተማመንበታለሁ። ማግኘት የሚፈልገው ዓላማውን ማሳካት ነው። ዓላማውም የግለሰቦች ተክለስብእና በማግዘፍ ሊደረስ እንደማይችል ጠንቅቆ ያውቃል። ዓቅም በፈቀደ ሠርቶ በማፍራት ማህበሩን ለማስተዋወቅ ግን ወደኋላ አይልም። የመጨረሻው የኢ.መ.ተ.ማ ግብ ዓላማዎቹን በማሳካቱ የሚጎናጸፈው ድል የሚመኝ እንጂ እነ እገሌን ወይም እነ እንትናን በመለማመጥ እግቡ ለመድረስ የሚሞክር ማህበር አይደለም። በመለማመጥ የሚገኝ ነገር መለማመጥ ሲያቆሙ በቀጭን ትእዛዝ መወርወርን እንደሚያስከትል የተገነዘበው ገና ድሮ መሆኑን ሊሰመርበት ይገባል።

እኔ፤ ኢ.መ.ተ.ማ ከመመሥረቱ በፊት ኤውሮጳ ውስጥ ሓሳቡ ሲወጠነጠን ውይይቱ ውስጥ ከተሳተፉት ሰዎች አንዱ ነኝ። በዛን ወቅት አጋጣሚ ሆኖ ቅርብ የሥጋ ዘመድ አብሮኝ የጀመረ አልነበረም። ቢኖር ግን በዓላማው አስፈላጊነት አምኖ እንዲገባበት ጠይቆኝ ሳይሆን እኔም ራሴ በውትወታ ባስገባው/ባስገባት የምደሰትበት እንጂ የሚከነክነኝ ምንም ነገር አይኖርም ነበር። በጎ ነገር ለማኅበረ ሰቡ ለማረግ የሚሳተፍ ሰው ሲገኝ አቅፎ መቀበል እንጂ፤ የኔ ቤተሰብ ስለሆንክ እነ እገሌ እንዳያሙን ወይም የእነ እገሌን ስሜት ላለመንካት ብዬ ተሳትፎውን ለመገደብ የሚያስገድደኝ ሁኔታ አልነበረም የለምም። ኢ.መ.ተ.ማ በራሱ ለሚተማመን ዓላማውን ለሚደግፍ ማነኛውም ሰው በሩ ክፍት ነው። ዓላማው ውስጥ እንከን አለበት የሚል ሰው ደግሞ ዐቅሙ ካለው፤ ኢ.መተማ የተቋቋመ ወቅት መቋቋሙን በማጥላላት በመድረክ ሳይወጡ ውስጥ ውስጡን አቧራ ለማስነሳት ቴሌኮንፈረንሶችን በሊቀመንበርነት እየመሩ ከነበሩት ውስጥ አንዱ አቶ ሥዩም እንደነበሩ ራሳቸው ያውቁታል። አሁን አቧራው ረግቦ ኢ.መ.ተ.ማ የራሱን ድርሻ በመወጣት ላይ ባለበት ውቅት እንደገና ሌላ አቧራ በማስነሳት ህብረተሰቡ ውስጥ ሌላ ውጅንብር ለመፍጠር መሞከር ግን የተበላ እቁብ የሚባለው ዓይነት ሆኖ ይታየኛል። የሆነ ሆኖ “ዝና ፍለጋ” የሚለው አባባል ከመስመር የወጣ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። እዚህ ላይ ሰው ሊል የሚችለውን እድምታ ነው ያሰፈርኩት የሚል ክርክር የሚያዋጣ አይሆንም። ኢ.መ.ተ.ማ ማን እንደሆነ በርግጠኝነት አላውቀውም፤ ስለሆነም ፍርዱን ለኢሮብ ህዝብ ተቸዋለሁ ያሉት ላይ ግን በትክክል እስማማለሁ። ኢ.መ.ተ.ማን የራሳቸውን ፍላጎትና እምነት በማስቀደም ያልሆነውን ነህ ብለው አይፈርጁት የሚለው ነጥብ ነው የሚያከራክረን እንጂ፤ ህዝባችንማ በጥሩም ሆነ በመጥፎ ኢ.መ.ተ.ማን የመፈረጅ የማይገሰስ መብቱ እንዳለው እኔም አምናለሁ። የሱን ፍርድ ከመቀበል የማምለጥ እድልም እንደሌለ አውቃለሁ፤ ሁላችንም ይችን ብናውቃት እጅግ ጠቃሚ ነው እላለሁ።

በተጠቀሰው የአቶ ሥዩም በረሀ ጽሑፍ ውስጥ የመጨርሻው አራት መስመሮች ለአቶ በየነ ገብራይ የተላለፈ ጥሪ አለ። ለአቶ በየነ ያለቸውን አክብሮት ከገለጹ በኋላ አቶ በየነን ምክር ብጤ ይለግሷቸዋል። ይኸውም፤ ከኢ.መ.ተ.ማ አባልነት ራሳቸውን እንዲያገሉ እስከመጠየቅ የደረሰ ነው። አቶ በየነን ለህዝብ ሲሉ በከፈሉት መስዋእትነትም ሆነ በአጠቃላይ ተግባራቸውና ስብእናቸው ከማከብራቸው ውድ የህዝብ ልጆች አንዱ መሆናቸው እኔም እመሰክራለሁ። አቶ በየነን እዚህ ቡድን ይግቡ ከዛኛው ራስዎን ያግልሉ፤ ለማለት ግን መብቱ አልተሰጠኝም። ከዛም አልፎ እንደ ታላቅ ድፍረት ስለሚቆጠርብኝ አልቃጣውም። ለነገሩ አቶ በየነ ኢ.መ.ተ.ማን “ሀ” ተብሎ ሓሳቡ መንሸራሸር ሲጀምር ከጀመሩት ውስጥ አንዱ በመሆናቸው የአቶ ሥዩም ጸሎት መስመሩን ያጠራጥረኛል። የሆነ ሆኖ ግን የግል እምነቱን ቀርጾ፤ የሚያምንበትንና የማይቀበለውን ሓሳብ ለይቶ ሕወቱን በትግል

ላሳለፈ ጉምቱ የፖለቲካ ሰው እንዲህ ዓይነት ምክር መለገስ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው እንደየግለሰቡ ሊለያይ ይችላል። በበኩሌ ግን አልሞክረውም። ሆኖም የተኛውም ይሁን የባለቤቱን ምርጫ አከብራለሁ። ምርጫቸውን ማክበር ማለት ሓሳባቸውን መቀበል ወይም መደገፍ ማለት አይደለም። በሓሳብ ተለያይተህ መከባበር ይቻላል። አቶ በየነን እማከብራቸው በሓሳብ ከኔ ጋር ስለሚሰማሙ አይደለም። የሚያስከብራቸው ሥራ ስለሠሩ ነው እማከብራቸው። በመሆኑም የአቶ ሥዩም ጸሎት እንኳ ቢሰምር ለሳቸው ካለኝ አክብሮት ቅንጣት ታክል አይቀነስም።

በመጨረሻ ለማለት የሚፈልገው ነገር ቢኖር፤ የአቶ ሥዩም ጽሑፍ እንደ እጥረቱ ሳይሆን ሰፊ እድምታ ያለው እንደመሆኑ መጠን እጅግ ሰፊ ትችት ሊቀርብበት የሚችል ነው። ሆኖም፤ ከቀረበው ጽሑፍ ለመውጣትና ቅርንጫፎችን እየነተተኩ ማስፋትም ስላልፈለግኩ ለጊዜው ጽሑፌን በዚህ ለመቋጨት እገደዳለሁ።

በሰፊው ለመመለስ የሚገፋፋ ትንኰሳ ሲመጣ ደግሜ አገኛቹሃለሁ!!

አንድነታችን ይጠንክር! ነገሮችን በአመክኒዮአቸው መርምረን ለመፍረድ ያብቃን!!

ሰኔ 30፣ 2006 ዓ.ም

For contact: ghirmay_g@hotmail.com